# የኢትዮጵያ እና የልጆቿ እውነተኛ ማንነት፡ በቀደሙት የፈረንጆቹ ደራስያን መጻሕፍት ተመዝግቦና ተከሥቶ ሲነበብ።

---

# ታዲያ፡ እውነታው ይህ ከኾነ፡ የዛሬዎቹ፡ የፈረንጁና የኢትዮጵያው ትውልዶች፡ ከቶ፡ ኹለቱም፡ ምን ይሉ ይኾን!?

---

ኪዳናዊት እኅቴ፡ እመቤት ፍቅርተ፡ ትምህርታዊ ሙያዋን በሚመለከት በምታቀርበው፡ በመጨረሻው የምሁርነት ማዕርጓ ማረጋገጫ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ፡ ካቀረበቻቸው አርእስተ ጉዳይ መካከል፡ አንዱ የኾነውን ቍም-ነገር፡ Ethiopia: The Classic Case በሚለው፡ በእንግሊዝኛውና በሌሎቹ መጻሕፍቴ ውስጥ ተካትቶ ከተብራራው የእግዚአብሔር እውነት ጋር በማስማማት ለመግለጽ ስለምትችልበት ኹኔታ፡ በቅርቡ፡ ስልክ ደውላልኝ ተወያይተን ነበር።

ቍም-ነገሩም፡ “ፈረንጆቹ፡ UTOPIA የሚሉት ስያሜ፡ የ<u>ኢትዮጵያ</u>፡ ሌላኛው አጠራር ነው! እነርሱ (ፈረንጆቹ) ኹላቸው፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በያገራቸው፡ ለሥልጡንነት በቅተው፡ Democracy በሚል ዘይቤ እየሠሩበት ያለውን፡ የማኅበራዊውንና ሕዝባዊውን፥ ብሔራዊውንና መንግሥታዊውን ሥርዓታቸውን፣ የቀረውንም መልካም ይትበሃላቸውን፥ ሃይማኖታዊውንና ዘውዳዊዉን ሳይቀር ያገኙት (ለምሳሌ፡ የዛሬዪቱን እንግሊዝን፡ በምሳሌነት ብንጠቅስ፡) <u>ከኢትዮጵያ፥ ከኢትዮጵያውያንና ከኢትዮጵያውያት</u> ነው!” የሚለው፣ በዚያ፡ በእንግሊዝኛውና በ"ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"፥ በሌሎቹም መጻሕፍቴ ውስጥ ሳይቀር የሠፈረው ኃይለ-ቃል ነው።

በስልክ ንግግራችን ጊዜ፡ እኔ፡ እነዚሁኑ መጻሕፍቴን ያዘጋጀሁት፡ እርሷ፡ ለጥናት ጽሑፏ ፈልጋ ያገኘችውን፡ UTOPIA የሚለውን፡ ኹለት ጥራዝ ያለውን፡ የእንግሊዛዊዉን የSir Thomas Moreን መጽሓፍ፡ አስቀድሜ አንብቤ እንደጻፍኩት የሚያስመስል፡ ፍጹም የመልእክት አንድነት ያገኘችበት መኾኑን፡ በአግራሞትና በአድናቆት ገለጸችልኝ፤ እኔም፡ ከደራሲው ስም በስተቀር፡ የተጠቀሰውን ድርሰት፡ በጭራሽ ያላየሁና ያላነበብሁ መኾኔን አስረዳኋት።

"ይልቅስ፡ ከቻልሽ፡ ይህንኑ መጽሓፍ ላኪልኝ!" ብዬአት ስለነበረ፡ እርሷም፡ የመጽሓፉን ኹለት ጥራዞች ማታውኑ፡ በኆዋው አውታር ላከችልኝ፤ የመሸኛው እ-ጦማርዋ ቃል፡ እንዲህ የሚል ነበር፡-

Attached with this email are the two books of Sir Thomas More. I only read book II. I noticed book I is also available online; so I've included it here.

From a glance, it looks like book I is about the original aspiration of British men for an English Commonwealth.

They are very interesting confirmations of the early plot to transfer the administrative system of the Holy Covenantal Ethiopianhood to British Commonwealth.

በምርምሩዋና በጥናቷ የቀጠለችው እመቤት ፍቅርተ፡ በዚሁ በተጠመደችበት የግዳጅ ኺደት ላይ ሣለች፡ ተመሳሳይ መልእክትን የያዘ፥ ነገር ግን፡ "The City of the Sun" በሚል ስያሜ፡ Tommaso Campanella በተባለ ደራሲ የተዘጋጀ፡ ሌላ መዝገበ ጽሑፍን ስላገኘች፡ ይህንኑ መጽሓፍ፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ እንዲህ ከሚለው እ-ጦማርዋ ጋር አያይዛ ላከችልኝ፡-

Here is yet another book (35 pages without copyright details) about the early Ethiopian administration and way of life; of course some details concealed and intentionally diverted. It is written by Tommaso Campanella.

This one is especially interesting because it details how the three divisions of the government in the "City of the Sun," which was led by a priest-king, are modeled after the Trinity of God ("Power," "Love," and "Wisdom"). It also explains the duties and responsibilities of the three divisions and the manner of their meetings. It is like "applied EthKOG Regulation."

I realized there are chain of works written in the 1600s by several Europeans about a righteous land the life style and administration of which they wanted to emulate. I don't know how many more works exist; but when I found a couple more, I stopped to be surprised.

Apparently, if one looks hard enough, the journey to re-construct the "lost" administrative system and mode of life is not as clueless as it seems, at least theoretically. They are generously releasing lots of classical works online. God bless them!

I thought you might enjoy reading it. It is beautifully written and spiritually uplifting!

የኹለቱንም ደራሲዎች መጻሕፍት ጥራዞች አንብቤ ስጨርስ፡ እኔም፡ የእርሷ አግራሞትና አድናቆት ተካፋይ ኾኜ፡ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነትን ምንነትና ማንነት በሚመለከት፡ የቃል ኪዳን ሕዝቡ ለኾኑት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በእኔ፡ ዝቅተኛ አገልጋዩ እጅ ላስተላለፈው መልእክቱ፡ ማረጋገጫ የሚኾን፡ ይህን የመሰለ፡ ተጨባጭ የእውነታ ማስረጃ፡ በሌላዪቱ አገልጋዩ አማካይነት የከሠተ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን፡ አመሰገንሁ።

እነዚህኑ፡ "ዩቶፕያ" የተባለውን፡ የሰር ቶማስ ሞርን የእንግሊዝኛ መጽሓፍ፡ ኹለት ጥራዞች፥ እንዲሁም፡ "ዘ ሲቲ ኦፍ ዘ ሰን" የተባለውን፡ የቶማሶ ካምፓኔላን፡ ባለአንድ ጥራዝ የእንግሊዝኛ መጽሓፍ፡ ለጎዋ-ሰሌዳችን አንባቢዎች፡ ኹሉንም፡ ይኸው፡ ከዚህ ጋር አቅርቤላችኋለሁ።

የኹለቱም ደራስያን መጻሕፍት ኢትዮጵያኛ ትርጉም፡ በፈቃደ እግዚአብሔር፡ ወደፊት፡ በጊዜው ታትሞ የሚሠራጭ መኾኑንም፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ልገልጽላችሁ እወድዳለሁ።

እንግሊዛዊው ሰር ቶማስ ሞር፡ እንደፈረንጆቹ አቈጣጠር፡ በየካቲት ፯ ቀን፥ ፲፬፻፸፰ ዓ. ም. ተወልዶ፡ ከደራሲነቱ ጋር፡ በመንግሥታዊ አስተሳሰብና አመራር ፈሊጠኛነቱ፡ በርካታ የቤተ ምልክናውን ሥልጣኖች የያዘ የመኳንንት ወገን ነበር፤ "ዩቶፕያ" የሚለውን መጽሓፉን፡ በ፲፭፻፲፮ ዓ. ም. አሳትሞ፡ ለሕዝብ ምንባብ ካበቃ በኋላ፡ በካቶሊካዊነቱ ምክንያት፡ በዘመኑ፡ የነበረው ንጉሥ ክብርና ሥልጣን፡ ከሮሙ የካቶሊክ ሊቀ-ካህናት (Pope) ክብርና ሥልጣን እንደሚልቅ የሚያረጋግጠውን ቃለ መሓላ እንዲፈጽምና ጽሑፍ ኪዳኑን እንዲያሠፍር ቢጠየቅ፡ ፈቃደኛ ባለመኾኑ፡ በለንደን ግንብ ወህኒ ቤት ታሥሮ ከቆየ በኋላ፡ በዕንቢተኝነቱ ስለጸና፡ የይሙት በቃ ፍርድ ተበይኖበት፡ በሓምሌ ፯ ቀን፥ ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ተሠየፈ።

እንግሊዞችም ኾኑ፡ ሌሎቹ ምዕራባውያን ተባባሪዎቻቸው፡ ሰር ቶማስ ሞር፡ ኢትዮጵያን፡ "ዩቶፕያ"፥ ኢትዮጵያውያንንም፡ "ዩቶፕያንስ" እያለ በመሠየም፡ የጻፈውን እውነተኛ ታሪክ፡ አገሪቱን፡ በደሴትነት፥ ታሪኩንም፡ በልብ ወለድነት አዘጋጅቶ እንዳቀረበው ለማስመሰል ያደረጉትን ሙከራና ጥረት፡ ምናልባት፡ ስለዚሁ ጉዳይ እየተከታተላችሁ፡ አንዳንድ ጥናትንና ምርምርን ለማካኼድ የምታስቡ ብትኖሩ፡ ድርጊታቸውን፡ በዚህ ገጽታው ጭምር ተመልክታችሁ፡ ነገሩን፡ በጥንቃቄ ልታስተውሉትና ልታመዛዝኑት እንደሚገባ ላሳስባችሁ እሻለሁ።

ሰር ቶማስ ሞር፡ መልእክቱ፡ በወገኖቹ ዘንድ፡ በቀላሉ ተቀባይነት እንዲያገኝለት፡ ይህን አቀራረብ፡ "ራሱ አድርጎት ይኾናል!" የሚለውንም፡ የመላምት አስተሳሰብ፡ እግምት ውስጥ ማስገባቱ ያስኬዳል።

ደግሞም፡ እኒሁ እንግሊዞች፡ በመቅደላ ተራራ ላይ፡ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ ካደረሱት ጥቃት የተነሣ፡

"'ገደልን!' እንዳይሉ፡ ሙተው አገኟቸው፤
"'ማረክን!' እንዳይሉ፡ ሰው የለ በጃቸው፤
"ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?
"ለወግ አይመቹ፡ ተንኰለኞች ናቸው።"

ተብሎ፡ በዚያን ጊዜዎቹ ኢትዮጵያውያን/ኢትዮጵያውያት የተላለፈባቸው የግጥም መልእክት መኖሩን በማወቅ፡ አኹን፡ በዚህ ረገድ እየፈጸሙ ላለው ድርጊት፡ አመልካች ምልክትነት ሊኖረው እንደሚችል ማስታወሱ አግባብ ይመስለኛል።

በምድር ላይ፡ "የሰው ልጆች" ተብለው ተፈርጀው ከሚርመሰመሱት ሕያዋን ፍጡራን መካከል፡ በቅዱሱ መጽሓፍ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብለው የሚታወቁት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ፍትሕ ርትዕ፥ ሰላምና ፍቅር፥ እውነትና ብልጽግና በሰፈነባት፥ አማልክትም፡ ዐብረዋቸው፡ በዓሎቻቸውን የሚያከብሩባቸው፥ የፍጹማን ሕዝብ መገኛ በኾነች፡"ኢትዮጵያ" በምትባል፡ ገናና መንግሥታዊ አገር የሚኖሩ ልዩ ወገኖች ስለመኾናቸው፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በነበሩት አያሌ ሺህ ዓመታት ውስጥ በተነሡት፡ ጥንታውያን የግሪክና የዓለም ፈላስፎችና ጸሓፊዎች ዘንድ፡ አያሌ ዝክረ-ነገር ተመዝግቦ ይነበባል፤ ይህም፡ እስከዛሬና አኹንም፡ ለምስክርነት እየቀረበ ይታያል።

ከአሕዛብ ብቻ ሳይኾን፡ በአብርሃም ልጅነታቸው እጅግ ከሚመኩትና ለስደት ከተዳረጉት አይሁድም ሳይቀር፡ የተመረጡ ዘሮች፡ ከየሃይማኖታቸውና ሥርዓታቸው ጋር መጠጊያና ማረፊያ ያገኙት፡ በዚችው ኢትዮጵያና በልጆቿ ዘንድ መኾኑ፡ በይፋ የሚታወቅ እውነታ ነው።

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ደግሞ፡ ቀደም ብሎ፡ ከመጀመሪያው የክርስትና መባቻ ዘመን አንሥቶ፡ ተሰዓቱ ቅዱሳን፡ ወደኢትዮጵያ እስከገቡበት፡ እስከስድስተኛው ምዕታመት ድረስ፡ በሃይማኖታቸው ምክንያት፡ የስደት ፈተናና የመከራ ቀንበር የወደቀባቸው ወገኖች ኹሉ፥ ክርስቲያኖች ሳይቀሩ፡ በመጨረሻ፡ የታመነና የተረጋገጠ መጠጊያንና ዕረፍትን ለመጐናጸፍ የቻሉት፡ በዚህችው "ኢትዮጵያ" በተባለችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በሰፈነባት አገር እንደኾነ፡ እስከዛሬ ገሃድ ኾኖ የሚታየው ግዙፍ ማስረጃ እነሆ ሲመሰክር ይገኛል።

ከዚያ ተያይዞ በቀጠለው፡ በሰባተኛው ምዕታመት የተነሣው፡ የእስልምና ነቢይና መሥራች የኾነው መሓመድ፡ በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም እምነት ያላቸውና በቸርነት ምግባራቸው የታወቁ፡ እውነተኞች ሕዝብ የሚኖሩባት እንደኾነች በማረጋገጥ፡ የተዋከቡና የባዘኑ ወገኖቹ፡ የሚያስተማምን ጥገኝነትን ሊያገኙ እንደሚችሉ አውቆ፡ እነርሱን የላከባት አገር፡ ይህችው፡ "ኢትዮጵያ" መኾኗ፡ የሚታበል አይደለም።

በመካከለኛው ዘመን፡ ፈረንጆቹ አውሮጳውያን፡ Prester Jan (ፕሬስተር ጃን) ማለትም፡ "ቄሱ ንጉሥ" በሚል ስያሜ፡ ይጠሩት የነበረው፡ ስመ-ጥርና ገናና መሪ ያስተዳድራት የነበረችው አገር፡ "ኢትዮጵያ" የምትባለው ምድር መኾኗ፡ በባዕዳኑ ምሁራንም ዘንድ የተረጋገጠ ነው። ሃይማኖታዊውና ምግባራዊው የእግዚአብሔር ሥርዓት ተመሥርቶባትና እውን ኾኖ የሚሠራባት፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሠፈረባትና የእግዚአብሔር መንግሥት አስተዳደር የተንሠራፋባት አገር፡ አዎን! ይህችው ኢትዮጵያ ናት። "Prester Jan (ፕሬስተር ጃን)" የተባሉትም፡ እውነተኛውን የመልከ-ጼዴቅን ሥርዓተ-መንግሥት ተከትለው፡ እስከ፲፪ኛው ምዕታመት መጀመሪያ ድረስ፡ ለ፫፻፴፫ ዓመታት የነገሡት፥ ዛሬ፡ በዓለም ላይ ድንቅና ብርቅ ኾነው፥ የላቀውንም የክብር ቅርስነት ደረጃ ተሸልመው፡ በገናናነት የቀጠሉትን፡ ከጭንጫ ዐለት የተፈለፈሉ ሕንፃ አብያተ-ክርስቲያናትን ያስገኙት፥ የአገው (ዛጔ) አጼዎች፡ እነቅዱስ ላሊበላ ናቸው።

በመጨረሻ፡ በአኹኑ፡ በሃያ አንደኛው ምዕታመት፡ እየታየ ያለውን ኹኔታ ደግሞ፡ እስኪ እንመልከት! ይኸውም፡ እነሰር ቶማስ ሞር እና ቶማሶ ካምፓኔላ፡ በየድርሳናቸው፡ አረጋግጠውና ገላልጠው ያቀረቡትን የጥንታዊት ኢትዮጵያን ሥርዓተ-ሕይወት፡ ማለትም፡ ኢትዮጵያ፡ ሕዝቧንና አገርዋን የምታስተዳድርበትንና የምትመራበትን፡ ሃይማኖታዊና ምግባራዊ፣ ማኅበራዊና መንግሥታዊ ባህል፡ በአንድ በኩል፡ የዛሬዎቹ ወገኖቻቸው፡ ኤውሮጳውያንና መሰሎቻቸው፥ አጋሮቻቸውና ተከታዮቻቸው፡ እንዴት አድርገው፡ ለየራሳቸው እየሠሩበትና እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ መመልከቱ ነው፤ በአንጻሩ ደግሞ፡ እኒሁ ወገኖቻቸው፡ የዚሁ ጠቃሚ ሥርዓት አመንጪና አበርካች የኾነችው አገር፡ ይህችውም ኢትዮጵያ፡ ከሕዝቧ ጋር፡ ከምድረ-ገጽ፡ ፈጽማ እንድትጠፋ ለማድረግ፡ እንዴት በትጋትና በብርታት እንደሚደክሙ መመልከቱ ነው። ይህንም እውነታ፡ ራሱን፡ ለአጥፊዎቹ ያስማረከው፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ከተቀረው፡ የዓለሙ ሕዝብ ጋር ዐብሮ፡ በአንክሮና በተዘክሮ እየተመለከተው ይታያል።

ለዚህ የተጨበጠ እውነታ፡ በአንድ ወገን፡ ራሷን፡ "ታላቋ ብሪታንያ" ብላ በመጥራት፡ ከዓለም መንግሥታት መካከል ቀዳሚ ያደረገችውን፥ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ የነበሩትንም አሕዛብ ጨምራ በማጠቃለልና ከኢትዮጵያ ያገኘችውን፡ "የጋራ ብልጽግና" የተባለ ኅብረተ-አህጉርን በመፍጠር፡ የዚህ አቋም ርእስ የኾነችውን፡ አገረ እንግሊዝን፡ በዘውድ ዙፋኗ ላይ ተቀምጣ የምትመራው የዳግማዊት ንግሥት ኤልሣቤጥ፡ ፷ኛ (ስድሳኛ) ዓመት የንግሥ በዓል፡ በዚሁ ፪ሺ፬ ዓመተ ምሕረት፡ ባለፈው ግንቦት ወር፡ ለአራት ተከታታይ ቀኖች፡ በታላቅ ዝግጅትና ድምቀት የመከበሩን ዜና፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የዛሬዋ ኢትዮጵያ፡ ከነሕዝቧ፡ ያሉበትን አሠቃቂ ኹኔታ፡ በማስረጃነት ማቅረቡና መመልከቱ ይበቃል።

እንግዴህ፡ "በደርግ እሥር ቤት ውስጥ ሣለሁ ያዘጋጀሁትንና አኹን፡ በእግዚአብሔር ቸርነትና ፈቃድ፡ ለኅትመትና ለሕዝብ ምንባብ በመቅረብ ላይ ያለውን፡ “አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!” የሚለውን፡ ባለሦስት ክፍል መጽሓፌን ረቂቅ ለተመለከታችሁት፡ ለአንዳንዶቻችሁማ፡ በዚህ መልእክት አማካይነት የተከሠተው ይህ አምላካዊ እውነታ፡ የቱን ያህልና ምንኛ ያስገርማችሁ! ያስደንቃችሁ!" በሚል ቃል እደመድመዋለሁ።

<u>የእግዚአብሔር እውነትና መንግሥት ኾና፡ ከታማኞች ልጆቿ ጋር፡ ለዘለዓለም የምትኖረው ኢትዮጵያ፡</u> ራሷን፡ ለሥጋዊው ዓለም፡ በበለጠ፡ ገሃድ እያደረገችና እያሳመነች መኼዷን ትቀጥላለች!

ንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
የእግዚአብሔር መንግሥቷ ኢትዮጵያ አገልጋይ።